# ችግራችንማ እኛው ነን !

## (አዲዮስ ዳያስፖራ)

ሀይለ ገብሬል ካሳ

የችግራችንን መንስኤ ፍለጋ ሩቅ መሄድ አያሰፈልገንም--ራሳችን ነን። በተለይ በባእድ ሀገር የምንኖር ዳያስፖራ የምንባለው ዜጎች ። በዚህ ሰሞን እንኳን በአንድ ግግር በሆነ ድር ገጽ የሰፈረውን ማስታውቂያ ብናይ እግዚ አ ማልት ያንስብናል ። ቅንጅትን ለመከፈል ለወያኔ አድሮ ስንት ጉዳት ያደረሰው ተመስገን ዘውዴ ሲያትል ከተማ መጥቶ ለዳያስፖራው ንግግር ያደርጋል ይላል ። በዚሁ ገጽ በቀኝ በኩል ደግሞ አንድ ጋዜጠኛነቱ በጥያቄ የገባ ግለሰብና አንድ የቀይ ሽብር ወንጀለኛ (ለ22 አመት ወያኔንም ያገለገለ) በጋራ በላስ ቬጋስ ገንዘብ ፍለጋ ዘመቻ ሊያደርጉ ይገኛሉ የሚልም ማስታውቂያ ግለሰቦቹን እያቆላመጠ ቀርቧል ። በወያኔ ይሁን በሌላ ዴ የሚል ፊደል የለጠፉትም በተቃዋሚ ሀይሎች ላይ የጭቃ ጅራቻቸውን ሲያጮሁ የሚያስተጋቡላቸው ወያኔን ተቃዋሚ ነን የሚሉት ድረ ገጾች ናቸው ።

በወያኔ ንግድ ላይ ማዕቀብ ይደረግ ሲባል ይህን የሚያፈርሰው ዳያስፖራው ነው ። በአሜሪክና ኣውሮጳ የወያኔ ቢራ፤ ጉደርና አክሱማይት ወይን፤የአዜብ እንጀራ፤ የጉና ኩባንያ ቡና በብዙ መደብሮችና ምግብ ቤቶች ይሸጣል ። ዋሺንግተን የነበረውና በወያኔ ቁጥጥር ስር ያለው አየር መንገድ ሁሌም ሞልቶ ሁሌም አትራፊ ነው ። ለኮንዶሚኒየም ቤት፤ ለመሬት ተመዝገቡ ሲባል የወያኔን ኤምባሲ የሚያጣብቡት በውጭ ሀገር የሚኖሩ ዜጎች ናቸው ። ነገ ወያኔ ሲተን የወያኔ ውሳኔዎች አብረውት እንደሚሄዱና እርምጃዎቹም እንደሚቀለበሱ ማውቅ አቅቷችዋል ። ወያኔውንም ሆነ ለወያኔ አድሮ ሀገር የበደለውንም፤ ዘረኛውንም ሆነ ኢትዮጵያን ገነጣጥየዬ ላጥፋ የሚለውን ሁሉ አይዞህ በርታ ባይና አስተናጋጅ ይሀው ዳያስፖራ የሚባለው ወያኔ አንድ የሚኒስቴር መስሪያ ቤት ያቋቋመለት ነው ። ከባዕድ ሀገር ኢትዮጵያኖች ወደ ሀገር የሚልኩት 4 ቢሊዮን ዶላር ደረሰ የተባለ

ገንዘብ የወያኔን ኤኮኖሚ ደግፎ የያዘ ነው ። ማነው ችግራችን? ራሳችን ። ከሁሉም በላይ ግን ጠባቂ ወይም በር  ያጣ በረት ይመስል ነብሩም ፍየሉም ፤ጅብም አህያም፤ ቀበሮና በጉም በአንድ የሚርመሰመስበት ሆኗል የፖለቲካው መድረክ። የዚህ ውጤት ደግሞ ግልጽ ነው-- በግና ፍየል አህያ ያልቃሉ--አውሬዎች ብቻ ይቀራሉ ። በሀቀኛ ታጋይ ድርጅቶች ላይ እየተዘመተና መድረኩ ለወያኔ ከፋፋዮች አጥፊዎች እየተከፈተ በመጨረሻ ታጋዮች ሲከስሙ አስመአዮችና ሆድ አደሮች ብቻ ይነግሳሉ ። ለዚህ ተጠያቂ በቅድሚያ ራሳችን ነን ። ወያኔና የወየነውን ሁሉ ማራቅ አቅቶናል ።የሀገር ቤት ድርጅቶች ራሱን ሰማያዊ ፓርቲ ብሎ ሊያደናግር የተነሳውንና የታውቁ ዓድርባዮች የገቡበትን ቡድን ከመሰረቱት ስብስብ ማስወገዳቸው ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል

ማመን ቢያስቸግርም አሁንም ከ22 አመታት ስቃይ በኋላ ከወያኔ ጋር እርቅን የሚሰብኩ አሉ ። የሚያደናግሩት ሳይሆን ከልብ በዚ የሚያምኑት ናቸው ዬእኛ ችግሮች። መደረግ የሚገባውን አመጽ ያደናቅፋሉና። በሌላ በኩል ግን ከማመጽ ማን አገዳቹሁ ከቻላችሁ ብለው ዕነሱም ሊመልሱ ይችላሉ ። ሰላማዊ ግን ነቅናቂ ሰልፎች በሙስሊም ወገኖቻችሁ ሲደረግ የት ገባችሁ ቢሉ መልስ አዳጋች ነው ። አይ ጸንፈኞች ናቸው የሚለውን የወያኔ ልፈፋ ተቀብሎ ፍርሃትን አቅፎ መቅረትን ማጠየቂያ መስጠት ቀላል አይደለም ። ወያኔን ሲታገሉ የተሰዉ አያሌ ናቸው። ከከንፈር መጠጣ ውጪ አላጀብናቸውም ። ይባስ ብሎ በወንጀለኛ ካድሬዎችና ወያኔ ባሰማራቸው ፈልፈላ ጋዜጠኞች ይወገዛሉ ። ክፍፍል ጎጂ መሆኑንና ህብረት ጠቃሚ መሆኑ እየታወቀ እያለ ድርጅቶችን ከውስጥም ሆነው ከውጭ ሊከፋፍሉ ሊያጠፉ የሚጥሩ ብዙ ናቸው ። ጉዳትም እያደረሱ ናቸው ። የድርጅቶችን ክፍፍል የሚያራግቡትን እረፉ ብሎ ማሳረፍ ሲገባ ወሬ ብለው የሚያስተጋቡና ቅራኔን የሚያባብሱ ጥቂቶች አይደሉም ። ተባበሩ ማለትን ሳይሆን ተሰባብሩ ማለትን ይበልጥ የሚያፈቅር ዳያስፖራ ቢባል ስህተት አይሆንም ። በህብረትሰቡ ውስጥ የሚወገዝ ተግባር የፈጸመን ይቅር በሉኝ ሳይል መልሶ ማቀፍና ከሕዝብ ጎራ ማስገባት በተደጋጋሚ የታየና ትግልን እየጎዳ ያለ ነው ። ሀረግሬሳ ከዘራ አይሆንም። ይህን መገንዘብ አቅቶን ነው ችግራችን አልወገድ ያለው ።